**ይድረስ ለ "ጊዜ መስተዋቱ" - ተስፋዬ ገ/አብ ማነው?**

**ደራሲ - ለአቶ ወልደሚካኤል መሸሻ**

**ባሉበት፡፡**

ከአቶ ተስፋዬ ሐቢሶ **13/02/2006**

ኢትዮሚዲያ - **October 1, 2013 – http://www.ethiomedia.com** ላይ ያሰራጩልዎትን ከዚህ በላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን መጣጥፍ እንደርስዎ ሁሉ በውጭ አገር ከሚኖር ወዳጄ አግኝቼ ያነበብኩት ገና ዛሬ ነው። ጽሑፉ በመጽሐፍ መልክ ሲታተም ምናልባትም በሰፊው ሊሰራጭልዎት ስለሚችል መጽሐፉን ያነበቡ ሰዎች ሂሳዊ ትችቶቻቸውን በዝርዝር እንደሚሰጡ እገምታለሁ።ይህ እስኪሆን ድረስ እርስዎም እንደገለጹት "ጊዜን መጠበቅ ይሻላል"፣ እውነትም ጊዜ መስተዋት ነውና! ይህንን ምላሽ ብጤ ለመጻፍ የተገደድኩት የእርስዎን ድርሰት ለመተቸት ሳይሆን "ሳያረጋግጡ ወሬ ፣ ሳይገድሉ ጎፈሬ" እንደተባለዉ በድርሰትዎ አጠቃላይ ጉዳዮች በሚለዉ ንዑስ ርእስ ስር እኔን በተመለከተ ያሰፈሩትና ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተዉ የተረት-ተረት ወሬ እንዲታረም ለመጠየቅ ነዉ፡-*"የወያኔ-ኢህአደግ ጊዜያዊ መንግስት በቻርተር ሲቋቋም ተስፋዬ ሃቢሶ የሃዲያን ህዝብ ወክሎ እምክር ቤት ከመግባቱም በላይ የምክር ቤቱ ፀሓፊ እንደነበርም የሚታወስ ነዉ፡፡ ታዲያም የፌደራል መንግስቱ ከህገመንግስቱ መዉጣት ጋር ሲቋቋም በምርጫ ያልተሳካለት ተስፋዬ ሃቢሶ ለወያኔ-ኢህአዴግ እጁን ሰጠ፡፡----እናም የሃዲያን ህዝብ በተለመደዉ መንገድ ለመያዝ ሲል ተስፋዬን በደቡብ አፍሪቃ የኢትዮጲያ አምባሳደር አድርጎ ሾሞታል፡፡ ተስፋዬ ገብረአብ በመባረር ይሁን በስራ ወደደቡብ አፍሪቃ ሲደርስ ተስፋዬ ሃቢሶ እዚያዉ ጠብቆታል፡፡ ምናልባትም ተገናኝተዉም ሊሆን ይችላል፡፡--------ከተስፋዬ ሃቢሶ ተነገረኝ የሚለዉን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሃዲያነት ነዉ፡፡ ተወርቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ነገር፡፡-------------------- ወዘተ፡፡*

ከሁሉ አስቀድሜ ላረጋግጥልዎት የምፈልገው እኔ እርስዎንም ሆነ አቶ ተስፋዬ ገ/አብ የተባለውን ሰው በፍጹም አላውቃችሁም። ፊት ለፊትም ሆነ በደብዳቤም ይሁን በሌላ የመገናኛ ዘዴ (ቴሌፎን ፣ ፌስቡክ ፣ ኢሜይል...ወዘተ) በጭራሽ ተገናኝተን አናውቅምና የእርስዎ የተሳሳተና የሽሙጥ አጻጻፍ እንዲሁም የተስፋዬ ገ/አብ "የቆርጦ-ቀጥል" ውንጀላ ለሁለታችሁም ያልተጠበቀ ትርፍ የሚያስገኝላችሁ ከሆነ ቀጥሉበት። በኔ እምነት ውጤቱ ጊዜያዊ ትርፍ የሚያስገኝላችሁ ቢሆንም ውሎ አድሮ ግን ኪሣራና ትዝብት እንጂ ፋይዳ እንደሌለዉ ከቶውንም አይጠራጠሩ፡ ሁላችንም ስለሌላ ሰው ለዚያውም በቅርብ ስለማናውቀው ግለሰብ "የቆርጦ - ቀጥል" ወሬ ስናስተጋባ በተቃራኒው ጎራ አያሌ ታዛቢ ሰዎች ደግሞ እንደሚኖሩ መጠራጠር እንደሌለብን አንድ የተከበሩ የቀድሞ የፍርድ ቤት ዳኛ ይስታሉ ብዬ አልገምትምና! ይህንን ሐተታ ባጭሩ እዚህ ላይ ላቁምና ወደፍሬነገሩ እስቲ ልግባ፤

- በ**1983** ዓ.ም. የሽግግር መንግሥት በቻርተር ሲቋቋም የሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆንኩትና ቀጥሎም የምክር ቤቱ ፀሐፊ ሆኜ የተመረጥኩት የከምባታን ብሔረሰብ በመወከል ነበር። የሀዲያን ብሔረሰብ በመወከል አልነበረም ፤ ምንም እንኳ

ከማንም ሀዲያ ያላነሰ ሀዲያ መሆኔ ባይካድም! ዝርዝሩ ለጊዜው ባይወሳም ቢያንስ ቢያንስ አሁን በህይወት የሌለች ዉድ እናቴ ኩሩ ሀዲያ ነበረችና!

- የሽግግር መንግሥቱ ወቅት ሲያበቃ በጊዜው የነበረኝን ተግባርና ኃላፊነት ለአዲሶቹ የኢህአዴግ ተመራጮች አስረክቤ እቤቴ ነበር የተቀመጥኩት እንጂ እርስዎ እንደሚሉት ወደደቡብ አፍሪቃ በአምባሳደርነት ተሹሜ አልሄድኩም። ከዚያም የአጭር ጊዜ የቤት ቆይታ በኋላ በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ተቀጥሬ በድርጅትና ሥራ አመራር ዘዴ አገልግሎት ኃላፊነት ለሰባት ዓመታት አገልግያለሁ ፤ ከ**1988-1994** ዓ.ም. ድረስ ማለት ነው።
- ቀጥሎም በ**1994** ዓ.ም. በደቡብ አፍሪቃ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኜ ተሹሜአለሁ ፤በነዚህም የሁለት አመታት የቆይታዬ ጊዜ ተስፋዬ ገብረአብ የተባለዉን ሰዉ አግኝቼዉም ሆነ አነጋግሬዉ አላዉቅም፡፡ እንዲያዉም ግለሰቡ በወቅቱ በደቡብ አፍሪቃ ስለመኖሩ እንኳ አልሰማሁም፡፡ ከሁለት ዓመታት የደቡብ አፍሪቃ ቆይታ በኋላ ደግሞ በመንግስት ውሳኔና ሹመት ወደዩጋንዳ ተዛውሬ በአምባሳደርነት ለሁለት ዓመታት ሳገለግል ቆየሁ፡፡ ከዚያም በ1998 ዓ.ም. የሹመት ጊዜዬን ፈጽሜ ወደሀገሬ እንድመለስ የኢፌዴሪ መንግሥት በመወሰኑ ውሳኔውን አክብሬ ወደውድ ሀገሬ ተመልሼና የጡረታ መብቴን አስከብሬ ከቤተሰቤ ጋር ከሞላጎደል በምቾትና በሰላም እኖራለሁ።
- እርስዎን ከከፍተኛ ፍርድ ቤት እስከጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት እኔን ደግሞ በደቡብ አፍሪቃና በዩጋንዳ አምባሳደርነት የሾመን የኢህአዴግ ፓርቲና መንግሥት ነበር። የሾመንም እርስዎ እንደሚሉት **"**እጅ ስለሰጠን**"** **(**እጅ የሚሰጥ ምርኮኛ ብቻ ነዉ**)** ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታችን ለቦታው ብቁ ስለሆንን ነው ብዬ ነዉ የማምነዉ። ስለእርስዎ ባላውቅም እኔ ግን በወቅቱ የኢህአዴግ አባል አልነበርኩኝም ፤ አሁንም አይደለሁም (ምርኮኛ የሚሉት የድርጅት አባልነት ከሆነ)። የሆነ ሆኖ የአጼ ኃይለ ሥላሴም ሆነ የደርግ ፣ የኢህአዴግም ሆነ ሌላ አገዛዝ የሚመሠርተው **(**ምናልባትም እናንተ አሁን በየመገናኛዉ አማካኝነት እንደምትደነፉት ወያኔን ገርስሳችሁ የምታቋቁሙት**)** መንግሥት የሚሾሚቸው የመንግሥት ተጠሪዎች የአገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም **(national interest)** ማስቀደም እና የመንግሥቱን ፖሊሲዎች የግድ መፈጸምና ማስፈጸም ስለሚጠበቅባቸው ለበጎውም ሆነ ለክፉው የስራ ውጤት በየደረጃቸው ተጠያቂ ይሆናሉና በዚህ ረገድ ሁላችንም በተለይም እንደእኔ ሶስት አገዛዞችን ያገለገልን ባለስልጣኖች ለየዘመኑ አገልግሎታችን የየድርሻችንን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ለመውሰድ ዝግጁ መሆን የግድ ይሆናል። ስለዚህ ሁልጊዜ ለሰራናቸዉ ስራዎች ሁሉ---መልካምም ይሁኑ መጥፎ--- ተጠያቂ መሆናችንን ረስተን ያለፈውንና የቀደመውን ብቻ ማውገዙ ለማንም ፋይዳ የለውምና ከዚህ አጉል ባህል ብንላቀቅ ይበጃል እላለሁ፡፡ ስለዚህ በሽሽት ወደውጭ አገር ስለሄዱ **(**ጉዞዉ እንዴትና በማን ስፖንሰርሽፕ እንደዚያ በፍጥነትና በአስተማማኝ ሁኔታ ለእርስዎና ለቡድንዎ አባላት እንደተቀነባበረላችሁ ገና ያልተፈታ እንቆቅልሽ ቢመስልም**!) "**ከደሙ ንፁህ ነኝ**"** ብለው እንደጲላጦስ እጆችዎን በውሃ ሊታጠቡ ባይሞክሩ ይበጃል። **"**ጊዜ መስተዋቱ**!"** ዛሬም ፣ ነገም ፣ ተነገወዲያም የማይለወጥ ክስተት ነውና አንድ ቀን ሁሉንም ግልጥልጥ አድርጎ ያሳየናልና!

- ከዚህ በላይ በግልጽ እንዳስረዳሁ ፣ እኔ አቶ ተስፋዬ ገ/አብ ስለተባለው ሰው በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት የሚወሩትን ወሬዎች እንደማገኘውም ሰው ከምሰማ በስተቀር ግለሰቡን በጭራሽ አላውቀውም ፤በተጨማሪም ተስፋዬ ገብረአብ ትግራዋይ ይሁን ኤርትራዊ እኔ አላዉቅም፡፡ በጽሑፍም ሆነ በቃል ከእርሱ ጋር ስለፕሮፌሰር መስፍንም ሆነ ስለሌሎች ጉዳዮች ያደረግሁት ጭዉዉትም ሆነ ቃለመጠይቅ አልነበረም ፤ በጭራሽ! የፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን የብሔር ማንነት ከቶውንም አላውቅም ፤ እርሳቸውም በኢትዮጵያዊነት እንጂ በሌላ መለያና መታወቂያ ሊመነዘሩ እንደማይሹ ለተደጋጋሚ ጊዜያት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር በይፋ ሲገልጹ የቆዩ ሊቅ ስለሆኑ "ከባለቤቱ የበለጠ አውቃለሁ የሚል ቡዳ እንጂ ሌላ ሊሆን ስለማይችል" እኔ ቡዳ አይደለሁምና ፕሮፌሰሩ "ህዲያ" ናቸው ብዬ ይህንን የተሳሳተ መረጃ ለማንም ሌላ ሰው አልሰጠሁም ፤ ይህን ተናግሬም አስቤም አላውቅም። ከሁሉም በላይ የህዲያ ሕዝብ የፕሮፌሰሮች ችግር ስለሌለበት እርሳቸውን በጉዲፈቻም ሆነ በሞጋሳ ሥርዓት በህድያነት ሊያቅፋቸው የሚሻ አይመስለኝም ፣ እርሳቸው ቢፈልጉ እንኳን።
- በመጨረሻም አሁን ያሉት ገዥዎች በሚያራምዱት ፖሊሲ የተነሳ የኢትዮጵያ ህልዉና አደጋ ላይ እንደሆነ በተደጋጋሚ ያነሱት ጉዳይ በፍጹም የተሳሳተና መሠረት የሌለዉ አስተሳሰብ ነዉ፡፡ በኔ እምነት ሁላችንም እንወዳታለን የምንላት የውዷቷ ሀገራችን የኢትዮጵያና የሕዝቦቿ አንድነት በጽኑና በአስተማማኝ መሠረት ላይ የተገነባበት ዘመን ከ**1983** ዓ.ም. ወዲህ ባለው ዘመን ነው። ኢትዮጵያ በሐውርታዊ ሀገርና የአያሌ ብሔረሰቦች ፣ ቋንቋዎች ፣ ባህሎችና እምነቶች አገር እንደሆነች ሕገመንግሥታዊ ዕውቅናና ጥበቃ የተረጋገጠበት ዘመን ላይ ስለምንገኝ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነታችን "በክሮሼ የተያያዘ ብጣሽ ጨርቅ" ሳይሆን "በብረት-ላሜራ እየተገነባ ያለ ጽኑ ግንብ" እንደሆነ መገንዘብ አለብን። ምንም እንኳዋን ተግባራዊነቱ ገና አርኪ ባይሆንም! ይልቁንስ ይችን አገርና ህዝቦችዋን ለመበታተን እየታገላችሁ ያላችሁት እናንተ ህዝብን መሰረት ያላደረጋችሁና የተከፋፈላችሁ፡ እንዲሁም እኛ ካልገዛን ኢትዮጲያ የምትባል አገር ህልዉና በአደጋ ላይ ነዉ ብላችሁ የምትቃዡ የስደት ፖለቲካ አራማጆች እንደሆናችሁ እስካሁን የገባችሁ አልመሰለኝም! ይልቁንስ እኛን አገር ውስጥ የምንኖረውን ኢትዮጵያውያን የሚያስጨንቀንና የሚያሳስበን በተለያዩ ምክንያቶች አገራችሁን ለቅቃችሁ በውጭ አገሮች የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን አንድነትና ህብረት አጥታችሁ እርስ በእርስ ስትባሉና ስትቦጫጨቁ እንደምትኖሩ መስማታችንና መገንዘባችን ነው። ይህ ከሆነ የናንተ አቋም፡-እንዴት አድርጋችሁ ነው እነተስፋዬ ገ/አብና የመሳሰሉትን ሰላዮችና የሀገራችን ጠላቶች በአንድነት የምትታገሏቸው? ለገዛሀገራችሁስ ልማትና እድገት እንዴት በጽኑ አንድነትና ህብረት ልትቆሙ ትችላላችሁ? ይህ ነው የኛ ጭንቀትናብሶት።ይህንን መጣጥፌን ስደመድም፡- "ግለሰቦችን የዉይይት ርእስ አድርጎ ማብጠልጠል የምጡቅ ምሁራንና ሊሂቃን እንዲሁም የበሳል ሰዎች ባህርይ አይደለምና" ከዚህ አጉል ጠባይ መላቀቅ ለሁላችንም ይበጃል እላለሁ፡፡ ቸር ይግጠመን፡፡

  – እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ይባርክ!

– **“ጊዜ መስተዋቱ!” ዛሬም ነገም ተነገወዲያም።**